የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፬
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.84
Addis Ababa 28th Jun, 2024

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር፻፸፬/፪፻፲፮**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቄራዎች ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ**

ገፅ…………………………………………… ፫ሺ፯፻፳፫

**CONTENT**

**Regulation no. 174/2024**
**Regulation issued to re-establish Addis Ababa City Government Abattoirs Enterprise**

Page……………………………………….….3723

## ደንብ ቁጥር፻፸፬/፪፻፲፮
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቄራዎች ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ ቄራዎች ድርጅት የእንስሳት እርድ አገልግሎት መሥጠትና ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን እንዲሁም ተረፈ-ምርቶችን አዘጋጅቶ ለሀገር ውስጥ እና ለውጪ ገበያ ጤናማ የሆነ እና ጥራቱን የጠበቀ ምርት በማቅረብ የከተማ አስተዳደሩን ገቢ ለማሳደግ እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን ከወጣው ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና ፺፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## Regulation no. 174/2024
## Regulation issued to re-establish Addis Ababa City Government Abattoirs Enterprise

**WHEREAS,** it has become necessary to harmonize with the Regulation No. 159/2016 issued to Re-determine the conditions under which Public Enterprise are managed by the Addis Ababa City Administration and the Addis Ababa City Slaughterhouses provides animal slaughtering services and prepares meat and meat products as well as by-products and provides healthy and high-quality products to the local and foreign markets to increase the income of the city administration;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with sub Article (2) of Article 68 and sub Article (1) of Article 93 the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

ያንዱ ዋጋ
Unit price

**አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭**
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቄራዎች ድርጅትን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፸፬/፪ሺ፲፮ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **“ደንብ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ ነው፤

፪. **“ቦርድ”** ማለት በደንቡ መሠረት የሚቋቋም የድርጅቱ አንድ የሥልጣን አካል ነው፤

## ክፍል ሁለት
## ስለድርጅቱ መቋቋምና ዓላማ

**፫. መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቄራዎች ድርጅት (ከዚህ በኋላ “ድርጅት” እየተባለ የሚጠራ) የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የድርጅቱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን ይሆናል፤

፫ ድርጅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**፬. ዓላማ**

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. ንጽሕናው በሚገባ የተጠበቀና ጤናማነቱ ተመርምሮ የተረጋገጠ የእንስሳት እርድ አገልግሎት ይሰጣል፤

፪. የሥጋ ውጤቶችን አደራጅቶ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያቀርባል፤

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This regulation may be cited as “Regulation issued to Re- Establish Addis Ababa City Government Abattoirs Enterprise Regulation No. 174/2024’’.

**2. Definition**

In this regulation, unless the context otherwise requires:

1. "**Regulation**" shall mean the Regulation issued to Redetermine, Redefine and Lead the conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024;
2. "**Board**" shall mean a body of authority of the organization established in accordance with the Regulation;

## PART TWO
## THE ESTABLISHMENT AND OBJECTIVE OF THE ENTERPRISE

**3. The Establishment**

1. Addis Ababa City Government Abattoirs Enterprise (hereafter referred to as "Enterprise") has been established as a Public Enterprise by this regulation;
2. The Organization's Accountability will be to the Administration Authority of Government Public Enterprises of the Addis Ababa City Administration;
3. The Enterprise is administered in accordance with the Regulation issued to Redetermine, Redefine and Lead the Conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024.

**4. Objective of the Enterprise**

The Enterprise shall have the following Objectives:-

1. Provide animal staughering service whose hygine is properly maintained and whose healthiness is medically ascertained;
2. Supply meat products to domestic and foreign markets after having them processed,

፫. ከተረፈ ሥጋ የሚገኙ መሠረታዊ ተፈላጊነት ያላቸው ምርቶችን በብዛትና በጥራት በማዘጋጀትና በማምረት ለሃገር ውስጥ ገበያ ያቀርባል፣

፬. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ይተምናል፣ ያስከፍላል፡፡

፭. <u>**ድርጅቱ እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ**</u>

በከተማው በተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባር ላይ መሳተፍ፡፡

፮. <u>**ካፒታል**</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፭ ቢሊየን ፮፻፹፬ ሚሊየን ፱፻፸፩ ሺ ፩፻፳፭ (አምስት ቢሊየን ስድስት መቶ ሰማንያ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ አንድ ሺ ህ አንድ መቶ ሃያ አምስት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፭ ቢሊዮን ፴፪ ሚሊዮን ፩፻፴፩ ሺህ ከ ፴፱ ሳንቲም(አምስት ቢሊዮን ሠላሳ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሠላሳ አንድ ሺህ ብር ከ ሠላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) በዓይነት እንዲሁም ብር ፮፻፶፪ ሚሊየን ፰፻፵ ሺ ፩፻፳፭ (ስድስት መቶ ሃምሳ ሁለት ሚልዮን ስምንት መቶ አርባ ሺህ አንድ መቶ ሃያ አምስት ብር) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

፯. <u>**ኃላፊነት**</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰ <u>**ዋና መስሪያ ቤቱ**</u>

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በከተማው ውስጥ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፱. <u>**ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

3. Supply other products to domestic market by processing and manufacturing them, in quantity and quality, out of essential elements extracted from by products of meat.

4. Determine and receive changes for the service it provides.

5. <u>**Public Service Obligation that the Enterprise is Expected to Provide**</u>

Engage in a variety of volunteer activities across the city.

6. <u>**Capital**</u>

The authorized capital for the Enterprise is Birr 5,684,971,125.00 (Five billion six hundred eighty four million nine hundred seventy one thousand one hundred twenty five) Birr, of which Birr 5,032,131,000.39 (five billion thirty two million one hundred thirty one thousand Birr and thirty nine Cents) in kind and Birr 652,840,125.00 (six hundred fifty two million eight hundred forty thousand one hundred tewenty five) Birr was paid in cash.

7. <u>**Liability**</u>

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. <u>**Head Office**</u>

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere in other parts of the city as may be necessary.

9. <u>**Supervisory Authority**</u>

Addis Ababa City Administration Public Enterprises Administration Authority shall be the enterprise's Supervisory Authority.

**፲. የድርጅቱ አደረጃጀት**

ድርጅቱ:-

፩. የሥራ አመራር ቦርድ፤

፪. አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፤

፫. ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

**፲፩. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፲፪. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**10. Organizational Structure**

The enterprise shall have:

1. Management Board of the Enterprise;
2. One Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officers as necessary and;
3. The necessary staff.

**11. Duration of the Enterprise**

The Enterprise is established for an indefinite period of duration.

**12. Effective Date**

This regulation shall enter into force as of this 28th day of June, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of June 2024.**

**ADANECH ABIEBIE DESSA**

**MAYOR OF ADDIS ABABA**